# የሰፈራና መልሶ ማቋቋም ዘመቻ በጋምቤላ

ከሰኔ አጋማሽ እስከ ነሐሴ መጨረሻ 1977 ዓም
የ **<u>መላኩ አየለ ገድል</u>** ማስታወሻ

## መግቢያ

አራተኛ አመት ሲኒየር ሆነን ሚያዝያ ወር መጨረሻ አካባቢ ለሁለተኛው ሴሚስተር ፈተና ዝግጅት መግቢያ ይሆን ዘንድ ጥናት ጀምረን ሳለ፡ ስለ ተማሪዎች መዝመት ወሬ ይናፈስ ጀመር፡ ከላይብረሪ ተመልሼ ከዶርሜ ልጆች ጋር የሰማነውንና የምንገምተውን መረጃ እንለዋወጣለን፡ ዘመቻው ግንቦት አንድ እንደሚሆን ምልክቶች መታየት ጀመሩ፡ ዶክተር ታምሬ ሃዋንዶ (የሶይል ማኔጅመንት መምህራችን) አስተማመርና ለገበሬዎች ምን ማለት እንዳለብንና እንደሌለብን ሲነግረን ቁርጥ መሆኑ ገባን፡ አንዳንድ መምህራንም **"እዚህ ጋ አቁመን ቀሪውን ስትመለሱ ትማራላችሁ"** ይሉ ጀመር፡ የሴሚስተር አጋማሽ ፈተናዎችም ተሰረዙ፡ ተማሪዎችም ክፍል መግባት አቆምን፡ ቅርብ ቅርብ ያሉ ልጆች ወደ የቤተሰቦቻቸው ሄዱ፡ የተማሪው ትምህርት ማቆም ስላሳሰበው ዲኑ ዶክተር መንግስቱ ሁሉቃ ወደ ትምህርት እንድንመለስ ማስጠንቀቂያና ማስፈራሪያ ማስታወቂያ አወጣ፡ ልዩ የስም ቁጥጥርም ተጀመረ፡ የተለያዩ ወሬዎች ሲናፈሱ ሳምንት አልፎ ሳምንት ተተካ፡ በግድ ትምህርቱን ብንከታተልም የማጥናት ሞራል ግን አልነበረንም፡ ወደ ሶስተኛው ሳምንት ላይ በስቲሙላንትም በምንም እያልን ጥናታችን ሞቅ ማለት ጀመረ፡ ታዲያ **ግንቦት 22** አካባቢ አንድ ምሽት ላይ **"በከፍተኛ ትምህርት ኮሚሽን ስር ያሉ ተቋማትና የመምህራን ማሰልጠኛ መምህራን ተማሪዎችና ሰራተኞች ለሰፈራ ፕሮግራም የመልሶ ማቋቋም ዘመቻ ሊዘምቱ ነው"** የሚል ዜና ስንሰማ የተወራው ወሬ ሁሉ እርግጥ መሆኑን አምነን ተቀበልን፡ እንቅስቃሴውም ከሰኔ 1-5 መሆኑን ካልተረጋገጡ ምንጮች ሰማን፡ ከሬድዮው በኋላ ጥርጥር ስለሌለ ደብተሮቻችንን ወርውረን ሸርጥና ቱታዎች አወላልቀንና ልብስ ለባብሰን ወጣን፡ ሌሎቹም ተማሪዎች እያፏጩና እየሮጡ ወደ ቴሌቪዥን ቤት ሲሄዱ ያልሰሙት ግርግሩ ግራ አጋብቷቸው በመደናገጥ ወጣ ወጣ ብለው ይጠይቃሉ፡ በማግስቱ ልዩ ልዩ ማስታወቂያዎች ተለጠፉ፡ የእንቅስቃሴው ቀን ማለትም **ግንቦት 30** ድረስ ትምህርት እንዳይቋረጥ ቢነገርም ቅሉ አልተሰራበትም፡ ብዙ ተማሪዎች በተለይ የሐረርጌና የአአ ልጆች ወደየቤታቸው ቢሄዱም እኔ ከግቢ ሳልወጣ ቆየሁ።

## ምድብና ጉዞ

የአለማያ እርሻ ኮሌጅ ተማሪዎች ጋምቤላ የተመደብን ሲሆን የሳይንስ ፋከልቲ በከፊል የቴክኖሎጂ፣ የጅማ እርሻ ኮሌጅ ና የህክምና እንዲሁም TTI እና አስመራ ዩኒቨርስቲ፣ በድምሩ 12,000 የሚሆኑ ዘማቾች በጋምቤላ መመደባችን ታወቀ፡ ከጉዞአችን በፊት ወደ ቤት ድሬዳዋ ቤተሰብ ጋ የሄድኩት በደከመች መኪና ራይድ አግኝቼ ስለነበር አቧራው ሸፍኖኝ እና የደንገጎ መንገድ እየናጠ ሰውነቴ ዝሎ ነበር፡ ቤተሰቤ አዋራው ቀያይሮኝ ሲያዩኝ በመደናገጥ እስካስረዳቸው ድረስ ደንግጠው በጉጉት ሲጠባበቁ የሆነውን ሁሉ አስረዳኋቸው፡ ዘመቻ እንደመሆኑ መጠን የሚያስፈልጉ አንዳንድ ነገሮች ተዘጋጅተውልኝ ገንዘብም (70 ብር አካባቢ) ተሰጥቶኝ ወደ ግቢ ተመለስኩ፡ እህቴ ዳቦ ቆሎ አዘጋጅታ ከሌላ ጓደኛዬ ጋር ግንቦት 29 ሐሙስ ዕለት አለማያ ድረስ አመጡልኝ፡ ፍራሻችንን መሬት አውርደን ቤቱን ሞልተን ፈረሽን (ምን ተፈርቶ? ማን ጠያቂ አለና?)፡ ክትባትም የወሰድነው በዚሁ እለት ነበር፡ ቅዳሜ ሰኔ 1 ቀን የመሄዱ ወሬ ግን እየቀዘቀዘ በመምጣቱና ምንም ማስታወቂያ ባለመኖሩ መቆየታችን አይቀሬ መሰለ፡ ባሉት ጊዜያት ከተለያዩ ጓደኞች ጋር መዋልና መዝናናት ተያያዝኩ፡ ሰው ሁሉ በጉጉት ሲቀርበንና ሲንከባከበን ላየ፣ የምንሄደው ወደ ጦር ሜዳ እንጂ ለጎጆ ስራ አይመስልም ነበር፡ ታዲያ ቀኑ 'ዛሬ ነገ' እየተባለ ሳይታወቅ በማለፉ ተማሪዎች ግቢውን ለቀው መውጣት ጀመሩ፣ የያዝነው ገንዘብም ዶርም ውስጥ፣ አለማያና ባቴ በመዝናኛ አለቀ፣ ሲቸግረኝ ወደ ድሬዳዋ ሄጄ ለመጠበቅ ወሰንኩ፡ ከቀትር በፊት ከቤተሰብና ከጓደኞች ጋር ከሰዓቱን ደግሞ በብስክሌት መጋላ እየወጣሁ መረጃ በማሰባሰብ አሳልፋለሁ፡ የአለማያ ተማሪዎችን ምስራቀ ፀሐይ ባር (ከዚራ) እየሄድኩ ነበር የማገኘው።

እንዲህ ቁርጡ ባልታወቀ ሁኔታ ጥቂት እንዳሳለፍን በሬድዮ '**የሸዋ ዘማቾች ወደ መተከል ጉዞ እንደሚያደርጉና ሌሎችም ተቋሞች የሚጓዙበት በየተቋማቸው ይገለፃል**' የሚል ነገር ተሰማ፡ ከዜናም ከሰውም ወሬ እየተከታተልን ሳለ የመጀመሪያው እንቅስቃሴ ሰኔ አጋማሽ አካባቢ መሆኑን ዜና እንደሰማሁ በማግስቱ ለመሄድ ስነሳ መንገድ ትራንስፖርት የምትሰራ ዘመዴ አስጠርታኝ '*መኪና እንድናቀርብ የተጠየቅነው ከሰኔ 19-23*' መሆኑን ስትነገረኝ እስከ ቀኑ መቃረቢያ ድረስ ድሬዳዋ ለመቆየት ወሰንኩ፡ ሰኔ 17 ቀን (ሰኞ) ወደ ግቢ ስገባ 'ለምን መጣህ?' ብለው አስደነገጡኝ፡ ለካስ ሰኔ 19 የሚጓዙት የ2ኛ አመት ተማሪዎች ብቻ ነበሩ። የዘመቻው መጓተት ጭራሽ እንድንጓጓ

አደረገን፡ ደግሞም ተመልሰን ማሚያ መማር ስለነበረብን የመመሪቂያ ጊዜአችን እንዲርቅ ባለመፈለግም ነበር፡ አሁንም የተባለው ቀን ሳይከበር ቆይቶ በመጨረሻ ዕሮብ እለት ማታ መኪኖች ወደ ኮሌጁ ሲመጡ ስናይ ተረጋጋን፡ ሐሙስ የመጀመሪያ ተጓዦችን በሌሊት ወጥተን ሸኘን፡ እኔና ጓደኞቼ ጭራሽ በተጠባባቂነት ተመድበን ስለነበር ወደ 30 የምንሆን ተማሪዎች ብቻ ግቢው ውስጥ ቀረን።

ዓርብ እለት ከሌሊቱ 10 ሰዓት የሚሄዱ ልጆችን እቃ ይዘን ወደ መሳፈሪያው ቦታ ስንደርስ ቦታው ከመጨናነቁ የተነሳ ሰው ፈልጎ ማግኘት አዳጋች ነበር፡ የኛም "ተጠባባቂ" መባል ግራ አጋብቶን ስንዋትት "ዕቃችሁን አምጡና ተጠባበቁ" አሉን፡ በችኮላ እርጥቡንም ደረቁንም ሻንጣችን ውስጥ ከተን እየተርበተበትን ብንደርስ ሌሎቹ ወደየተመደበላቸው ባስ ሲገቡ እኛ የ4ኛ አመት ዕፅዋት ሳይንስ ተማሪዎች ብቻ ውጭ ቀረን፡ ሙሴ ብቻ የውሳኔውን ድንገተኝነት በመቃወም 'አልተዘጋጀንም'፡ መሄድ የለብንም እያለ ይከራከር ነበር'፡ በኛም ይስቅብን ነበር፡ በመጨረሻ አንድ መኪና ቦታ አለው ተብሎ ሮጥን ብንሄድ ለማ ምትኩ ብቻ ለመግባት ቻለ፡ ሆኖም ግን እሱ የኔን ዕቃ እኔ ደግሞ የሱን ይዘን ስለነበር አስቁሞ ለመውረድ ተገደደ፡ እየተወዛገብን (በደስታም በብስጨትም) ተመልሰን ቁርስ በልተን ተኛን።

ለቀረነው ጥቂት ተማሪዎች ካፊቴሪያው የሚያዘጋጀው ምግብ እጅ የሚያስቆረጥም ሆኖ አገኘነው፡ የአመቱን ቁጭት ለመወጣት ወይስ ያሙቱን በጀት ለመጨረስ? መጀመሪያ የወሰድነው ምግብ ራሱ አያልቅም እንጂ ድጌ መሄድ የሚከለክል የለም፡ ከሰዓት ዶርም ውስጥ ምሽት ባቴ ከተማ እያመሸን እንገባለን፡ ቅዳሜ ጠዋት ተኝተን አረፈድንና ምሳችንን ጨጓራችን እስኪወጠር በላን፡ ቅዳሜ ማታ ዕቃቸንን አዘጋጅተን እሑድ በሌሊት ከሚዘምቱ ሰራተኞች ጋር በመኪና ወደ ድሬዳዋ አየር ማረፊያ ተጓዝን። የሰራተኞች ሸኝዎች መኪና ተመድቦላቸው መጥተው ስለነበር ማረፊያው ውስጥ አብረን ትንሽ እንደቆየን ወጡ፡ ሌሎችም ተማሪዎች ከTTI ነበሩ፡ ተፈትሸን ስንጨርስ አውሮፕላኖች ቀረቡና ከጥዋቱ 3፡30 በረራ ጀመርን፡ ከአንድ ሰዓት ተኩል ጉዞ በኋላ ጋምቤላ እንደምንደርስና በ14ሺ ጫማ ከፍታ እንደምንበር ተነገረን፡ አውሮፕላኑ አንቶኖቭ ነበርና ጨኸቱ ጆሮአችንን ስላደነቆረን ጆሮአችንን በጥጥ ወትፈን በዓይን ብቻ እየተያየን ቁጭ አልን፡ አቀማመጣችንም እንደ ዕቃ ወለል ላይ ሲሆን ግማሹ ቁጭ ይላል ግማሹ ይተኛል፡ ትንሽ እንደበረርን ብዙዎች ደካከሙ፡ እኔም ወደላይ ወደላይ የሚል ስሜት ሲመጣብኝና ላብ ሲያዘፍቀኝ ተከናንቤ ተኛሁ (መሀላችን ያስቀመጡት ባልዲም ሊሆን ይችላል ማቅለሽለሹን የፈጠረው)፡ አንድ ሰዓት ያህል እንደተጓዝን ወደ መስኮት ጠጋ ብዬ ባይ ደመና ብቻ ሆነብኝ፡ ለመድረስ 15 ደቂቃ ሲቀረን አውሮፕላኑ ዝቅ ስላለ የጋምቤላ መሳጭ አረንጓዴ ምንጣፍ ታየን፡ "አሁን ነው 'ለም ናት አገራችን' ማለት" አልኩ በልቤ፡ ወንዞች መንደሮች መንገድ እያየን ሳናስበው አውሮፕላኑ አረፈ፡ ዕቃችንን የሚጠባበቁት መኪኖች ላይ ጭነን ምሳ እስኪዘጋጅ እንጠባበቅ ጀመር፡ ጋምቤላ ከተማ 15 ኪሜ ያህል ትርቃለች፡ ለመቆያ ያህል ተዘጋጅቶ አብሮን የመጣውን ሳንድዊች በልተን ዋናው ምሳ ተዘጋጅቶ ጥብስ በዳቦ በልተን ጉዞአችንን ወደ ምድብ መንደራችን ጀመርን።

## ጊሎ አቦል ጣቢያ

አካባቢው በጣም ሞቃት ከመሆኑ ሌላ አፈሩ በጣም ጥቁርና መረሬ የሚባለው አይነት ነው፡ መሬቱ ሁሉ አረንጓዴ ለብሶ ማየቱ ግን ለብዙዎቻችን አዲስ ነበር፡ የሚበዛው እንደሰንበሌጥ አይነት ረጃጅም ሳርና ሁለት አይነት ዛፎች ናቸው፡ ሰባት ሰዓት አካባቢ ከማረፊያው ተነስተን ወደ ሰፈራ ጣቢያችን በመጀመሪያው መኪና ሆነን መጓዝ ጀመርን፡ በበረራው የደከሙና የታመሙ ልጆች ስለነበሩ ሙቀቱ ተጨምሮበት ተደባብረን ነበር የተጓዝነው፡ በግምት ከሁለት ሰአት የመኪና ጉዞ በኋላ '**ኡባላ**' ሰፈራ ጣቢያ የሚል አየን፡ ሌሎችም ጣቢያዎች እያለፍን ስንሄድ ተማሪዎች መንገድ ላይ ሲንገላወዱ እናይ ነበር፡ የአለማያ ተማሪ በሙሉ '**ጊሎ አቦል**' የሚባል ቦታ መመደባችንን ስንሰማ ቢያንስ የምናቃቸው ተማሪዎችን እንደምንቀላቀል በማሰብ ደስ አለን።

ሰኔ 23 እሑድ ከቀኑ 10 ሰዓት አካባቢ ጣቢያችን ስንደርስ ቀድመው የደረሱት ተማሪዎች በሙታንታ ብቻ ሆነው አንዳንዶቹም ስስ ሸሚዝ ወይም ከነቴራ ለብሰው በየጥላው ስር ቁጭ ብለው ይጠብቁን ነበር፡ ሲነግሩን ታዲያ ምግባቸው ኮሾሮ በቆርቆሮ ዝግን ወጥ መሆኑን፣ እስከ ምሽት ሁለት ሰዓት ድረስ አለመጨለሙን፣ ቢምቢ ሙብዛቱን፣ እባብም በገፍ እንደሚገኝ ነበር።

እንደደረስን የተመድብነው B-22 ዳስ ነበርና እኔ ሙሴ ለማ ተሾመ ኪሮስ መሐመድ ዳውድ በስተምዕራብ በኩል ጥጉን ይዘን መኝታችንን በመደዳ ያዝን፡ ቤታችን አጠገብ ሽንት ቤት በመኖሩ ችግር ይገጥመናል ብለን እንደፈራነው አልሆነም፡ ቤታችን የመጨረሻው ስለሆነ ቢምቢ ቢበዛበትም ንፋስ ጥሩ ያገኝ ስለነበር አልከፋንም፡ መንገድ

ስለደከመንና ራስምታትም ብዙዎቻችንን ስላመመን ትንሽ ዕረፍት ወስደን የምናድርበትን ለማዘጋጀት ሣር በማጨድ ዘመቻውን አሐዱ ብለን ጀመርን፡ በዛ ድካም በዛ ሙቀት ከቀን ሙሉ ጉዞ በኋላ ሻወር ወስዶ አልጋ ላይ መዘረር የህልም እንጀራ ሆነብን፡ ሣር ለማጨድ በላብ ተዘፍቀንና ቆዳችን ሽፍ ብሎ እየበላላን መኝታችንን ካስተካከልን በኋላ ለካ ገና እራት ማዘጋጀትም ነበር፡ ለሁለት ቀን የሚሆን ኮሾሮ ተከፋፍለን፣ ቀድመውን ከመጡት ልምድ በመውሰድ እራት ማዘጋጀት ጀመርን፡ በመጀመሪያ ኮሾሮው ይቀጠቀጣል፣ ቀጥሎ ጣሳው በማጭድም በምንም ተከፍቶ ይሞቅና ከኮሾሮው ጋር ተደበላልቆ በሹካ እየተነሳ ወደ አፍ ከገባ በኋላ በጥርስ ወጊነት፣ በምላስ ዘበኝነት በምራቅ አጃቢነት የጉሮሮን መንገድ ተከትሎ ወደ ጨጓራ እንደደረሰ፣ አንድ ኮዳ ውሀ ይከተለዋል፡ እንዳንተወው ሌላ ምንም ምርጫ የለም፡ በገንዘብ የሚገዛ ነገር የለም፡ እኛም ያለ ዳቦ ቆሎ የያዝነው ነገር የለንም፡ ካልበላን ወባውም ምኑም እንደሚጎዳነም በማሰብ እንኮመኩመው ገባን።

ከገባንበት ሰዓት ጀምሮ ውሀ በጣም እንጠጣለን፡ በጣም ስለሚያልብ ግን ሽንት የሚባል ነገር የለም፡ መሸትሸት ሲል በረድፍ ከሚገኙት በላስቲክ ከተሸፈኑት የላስቲክ ዳሶች ውስጥ የሚኖሩ ተማሪዎች በአንድነት ተሰብስበን ኮሾሮ ስንቀጠቅጥ ማየት ትዕይንት ነበር፡ ሲመሽ ቢምቢዎች በጣም ስለሚያስቸግሩ እሳት እናነድና ከበን የተሰፋ መቁረጥም የብስጭትም ይሁን ቅጥ አንባሩ የጠፋው ዘፈን ይዘፈናል፡ አስቂኝ ጉራማይሌ ግጥሞችም ይሰማሉ፡ እኔም ታዲያ ከጓደኞቼ ጋር እየተዘዋወርኩ የተለያዩ ትርዒቶችን በማየት አሳልፋለሁ፡ "እንደዚህ ነው ሁለት ወር የምንኖረው?" ብዬ ሳስብ እውነት እውነት አልመስል ይለኛል፡ መቀበል ግዴታ ስለሆነ የሚያስረሱ ነገሮችን እያደረጉ እራስን እያበረታቱ ጤናን እየተመኙ ከመኖር ውጭ ከደርግ ጋር ማን ይታገላል? የእሳት ዳር ጨዋታው ከጥምቀት ጋር ስለሚመሳልና በየቀኑ የተለያዩ ፈጠራዎች የሚታደሙበት በመሆኑ እየለመድነው መጣን፡ ሰፈራ ጣቢያችን አንድ የመንግስት እርሻ ስለሚገኝበት ከእርሻው የሚመጣ በጀነሬተር የሚመነጭ መብራት ስላለ ማታ ማታ ወዲያ ወዲህ ከሚንሸራሸረው ተማሪ ጋር ደማቅ ከተማ አስመስሎታል፡ እቤታችን ውስጥ መብራት ስለሌለን በዚህ በመንገድ መብራቱ እና በእሳቱ ነው የምንደሰተው፡ የአለማያን ብርድ ለመከላከል ጃኬት የማይለየው ሁሉ አሁን ወይ ራቁቱን ወይ በከነቴራ ሲሄድ ማየቱ ያስደምማል፡ የመጀመሪያው ቀን የእንቅልፍ ሰዓት ደርሶ ስንተኛ እኔ የቢምቢ መከላከያ ሲኖረኝ ሎሎቹ ሲቸገሩ አደሩ፡ ልብስ መከናነብም ሙቀቱ አይፈቅድም።

## የዘመቻው ሳምንታት

### ሳምንት 1

ሰኞ ዕለት ሰኔ 24 ቀን አልጋችንን እንጨት ቆርጠን አልጋ ለመስራት ተነስተን ወደ ጫካ ሄድን፡ ጋምቤላ ጠዋትም ቀንም ማታም ስለሚሞቅ በጣም ያልባል፡ አንድ ትንሽ ነገር ለመስራት ከተንቀሳቀሱ የሚፈሰው ላብ ጋራ የናዱ ወይም ድንጋይ የፈለጡ ያህል ነው፡ ነገሩ በኛ ጉልበት እንደማይሆን ስንገነዘብ ልብስ እንደ ክፍያ ተጠቅመን አኟኮቹን ለማሰራት ተስማማን፡ እኔ ካናቴራ፣ ተሾመ ሱሪ፣ ሰጥተን ለአራት ሰው አልጋ አሰራን፡ ሣራችንን (ፍራሽ) ገዝጉዘን ቢምቢ መከላከያ ደግሞ ልንለብስ ያመጣነውን ኩታና ጋቢ በመነጣጠል እንደ አጎበር ሰቀልነው፡ ከባዱን ስራ አቃለን አረፍ ከማለታችን ወደ 10 ሰአት ላይ ስብሰባ ተጠርተን በማግስቱ ስራ እንደምንጀምር ተነገረን፡ ገና አንድ ቀን ማደራችን ስለነበረ ቶሎ የሚያስጀምሩን አልመሰለንም ነበር፡ የመጀመሪያው ስራችን ካፊቴሪያ መጠገን ነበር፡ የሚቀጥሉትን ሁለት ቀናት በሳር አጨዳ ላይ ተሰማራን፡ መጀመሪያ ላይ እንሰራ የነበረው በየአመታችን እና ዲፓርትመንታችን ተቧድነን ስለነበር በስራ ወቅት የነበረው ጨዋታና ቀልድ ደስ ይል ነበር፡ በሄድን በ5ኛው ቀን ካፊቴሪያ ሻይ ተፈልቶ እንድንጠጣ የተጠራን ጊዜ ተማሪው የሮጠው ሩጫ አይረሳኝም፡ ያንኑ እለት ማታ ካፊቴሪያው እራት አዘጋጅቶ ከኮሾሮ ገላገለን፡ በመጀመሪያው ሳምንት መጨረሻ ላይ ከሁሉም ዲፓርትመንትና ከሰራተኛ የተቀላቀለበት አዲስ ምድብ ሲወጣልን እኔ በቡድን 2፣ ንዑስ ቡድን 7 አባል ሆንኩኝ።

### ሳምንት 2

በአዲሱ ምድብ ሆነን የቤት ስራ ላይ ተመደብን ስራ ጀመርን፡ የቤቱ ስራ ፕሮሲጀር መጀመሪያ 20 ጉድጓድ በሰርክል አስሩ በ30 ሴሜ አስሩ በ50 ሴሜ ጥልቀት ተቆፍሮ ባላውና ምሰሶ ይተከላል፣ ቀጥሎ ሶስት ማገር ለቋሚው ይማገራል፣ ጣሪያው መሬት ላይ ተሰርቶ ይሰቀልና ይማገራል፣ በዚሁ ከሳር ክዳን በስተቀር የቤቱ ስራ ሲጠናቀቅ እናስመዘግባለን፡ በምድባችን ካሉት ልጆች ውስጥ የማውቃቸው በጣም ጥቂቶቹን ብቻ ሲሆን ንዑስ ቡድናችን ውስጥ ያለነው 50 ሰዎች በ5 ዩኒት ሲደለደል በሙሉ ከማላውቃቸው 9 ተማሪዎች ጋር ደረሰኝ፡ እንደበፊቱ ጨዋታና ቀልድ ባይኖርም ሁላችንም ቁጭ ሳንል እየተረዳዳን ስራውን እናጣድፈው ገባን፡ እየዋለ ሲያድር እየተግባባን መጣን፡

ከባድ ችግር የሆነብን የምግብ ሁኔታው ነበር፡ ሁሌም የሚሰራው ሩዝ መኮሮኒና ፓስታ፣ ለዛውም ምንም የማይጣፍጥ ሲሆኑ (ያው ግብዓቱም ችግር አይደል?) ይባስ ብሎ መጠኑ ራሱ በቂ አልነበረም፡ ሆኖም ግን በጥራት ጉድለት የተነሳ የተሰጠውን ጨርሶ የሚበላ ሰው ብዙ አልነበረም፡ ትንሽ ጎራርሰን ውሀ ብዙ ስንጠጣ ሆዳችን የሞላ ይመስለናል፡ ስራ ቦታ ሄደን ትንሽ እንደሰራን ጉልበታችን ይዝላል፡ መጥረቢያም ሆነ መቆፈሪያ ማንቀሳቀስ ይሳነናል፡ ከስራ ወደቤት እንደተመለስኩ በውሃ አለቃለቅና (ገላ የምንታጠበው ሜዳ ላይ ነው) ትንሽ ካረፍኩ በኋላ ወደ ምግብ ሰልፍ እሄዳለሁ፡ ሰልፉ ሌላው ዘመቻ ሆነብን፡ በተለይ የምሳ ሰዓት ሰልፍ አድካሚና አሰልቺ ነበር፡ ረጅም ሰልፍ ላይ ቆይተን ሳለ የተሰራው ምግብ ስላለቀ እስኪበስል ጠብቁ ስንባል ደግሞ ሌላ ፈተና፡ ያለበቂ ዕረፍት ወደ ከሰዓቱ ስራችን ለመሄድ እንገደዳለን፡ በዚህ ሁሉ ተግዳሮቶች ውስጥ ምን አይነት ስራ ሊሰራ እንደሚችል መገመት አያዳግትም።

በትርፍ ጊዜያችን ደግሞ ወደ አፏኮች ሰፈር እንሄዳለን፡ ሰፈራቸው በጣም ንፁሕና በፕላን የተሰራ ይመስላል፡ በራፋቸውን እንደጤፍ አውድማ ከማሳመራቸው የተነሳ እህላቸውን መሬት ውስጥ የተቀበረ ሙቀጫ ውስጥ በቆሎ ወቅጠው ዱቄቱን አውጥተው መሬቱ ላይ ነው የሚያረጉት፡ ብዙዎቹ ከትንሽ ብጣሽ ግልድሞሽ በስተቀር ራቁታቸውን ነው የሚሄዱት፡ ሕጻናትማ ጭራሽ ምንም አይለብሱም፡ ትላልቅ ሴቶች ጋያ ወይም ሲጋራ እያጨሱ ባለ 44 ጉድጓድ ገበጣ ይጫወታሉ፡ ቤታቸው ትንንሽ ጎጆ ሆና በሯ አጭር ስለሆነች ጎንበስ ተብሎ ነው የሚገባው፡ ደጋጎችና እንግዳ ወዳድ በመሆናቸው እስከመኘታ ቤታቸው ገብተን እንድናይ ይፈቅዱልን ነበር።

የለመድናቸው ምግቦች አይናችን ላይ ውል ሲሉ ማግኘት እንደማይቻል በመገንዘብ ለመርሳት እንሞክራለን፡ ስጋ ግን ለማግኘት እንደምንችል በወሬ ወሬ ሰምተን ማሰስ ጀመርን፡ ፍየል በልብስ እየቀየርን ለመብላት ሞክረን ሳይሳካልን ቀረ፡ ሌሎች ፍየል ጠብሰው ሲበሉ ስናይ አምሮቱ ባሰብን፡ በመጨረሻ ከአፏክ ወታደሮች ጋር ተነጋግረን በሁለት ብር ከ2 ኪሎ የማያንስ ቆርኪ የሚባል እንደ ድኩላ አይነት አውሬ ስጋ አገኘን፡ አንድ ሽንኩርት ጨውና በርበሬ ብቻ በመጠቀም ጥብስና ቅቅል ሰርተን የበላነው አቤት መጣፈጡ! አንዳንዴ በቆሎ እሸት በገንዘብ ወይም በሙታንታ (ከገንዘብ ሙታንታ ይመርጣሉ) ቀይረን ጠብሰን እንበላለን፡ አንደ እሑድ **ፑቻላ** የሚባል ሰፈራ ጣቢያ ሄድን፡ በዚህ ጣቢያ የሚገኙት የሐረር ፐፐ፣ የአስመራ ፐፐ፣ እና የጅማ ሜዲካል ቴክኖሎጂ በከፊል ነበር፡ አንዳንድ የምናቃቸው ልጆች አግኝተን ምሳ እዛው በልተን ተመለስን፡ በሳምንቱ አንዴ የሰፈሬ መላኩ የሚባል ልጅ ሊጠይቀኝ መጥቶ ሌላ መዝናኛ ስለማይገኝ ተሰባስበን ሬድዮ እየሰማን ጊዜ ማሳለፍ ቻለናል።

## ሳምንት 3

በሶስተኛው ሳምንት መጀመሪያ ላይ የሮሃ ባንድ እንደሚመጣ ተነግሮን በናፍቆት ስንጠባበቅ ከርመን ሐምሌ 10 ዕሮብ ቀን ከጠዋት ጀምሮ የተዘጋጀው መድረክ አካባቢ ተሰብስበን ፀሐይ ከወረደብን በኋላ ወደ አራት ሰዓት አካባቢ መጡ፡ አምስት ሰዓት አካባቢ ዝግጅታቸውን ጨርሰው ኮንሰርቱ ተጀመረ፡ ከታዋቂ ዘፋኞች ውስጥ መሀሙድ፣ ኩኩ፣ ኤፍሬም፣ ሐመልማል፣ ንዋይ ነበሩ፡ መሀሙድ ሙዚቃውን በአማሌሌይ ጀመረ፡ ከዛማ ዘፈኑ ቀለጠ፡ በጣም ብዙ ተማሪ እየዘለለ መድረክ ላይ ወጥቶ ይደንሳል፡ ዘፋኞችን አቅፈው ሲስሙና ሲንጠለጠሉባቸው ዘፈኑ ይሰናከላል፡ በተለይ ኤፍሬም "የኔማ" ን ሊዘፍን ሲወጣ ብዙ ተማሪ ስለተጠመጠሙበት መዝፈን ተሳነው፡ ወታደር መጥቶ ተማሪዎቹን ከመድረክ ላይ ካስወገደ በኋላ እንደገና ይጀመራል፡ ተማሪው በጣም ፈነጠዘ፡ የአስተዋዋቂዎቹ የታማኝና የልመንህ ቀልዶች በጣም አዝናኑን።

በዚህ ሳምንት ከባድ ዝናብ ዘንቦ ከስራ በመቅረታችን እፎይታ አገኘን፡ መረሬው ጭቃ ግን አላንቀሳቅስ ከማለቱ ሌላ የብዙ ሰው ጫማ ገነጣጠለ፡ ሙቀቱን አስታገሰልን ስንል መረሬው ጭቃ ደግሞ ሌላ ችግር ሆነ፡ ሶስተኛዋን እሑድ በርጫ ወይም ፊልም ወይም ቲያትር በማየት ሳይሆን ጊሎ አቦል ወንዝ ዳርቻ በመሄድ የሚዋኙትን ስናይ ወይም ልብስ ስናጥብ በየጓደኞችም ድንኳን በመሄድና በመጠየቅም ነበር ያሳለፍነው፡ እሑድ መሸትሸት ሲል የሰኞ ስራችን ይታወሰንና ሀሳብ ይገባናል፡ ቅዳሜ ምሽት ግን ምርጥ ናት - ለምን? ጠዋት መነሳት ሰለሌለ፡ በዚህን ሰሞን በምግብ መበላሸት የተነሳ ተማሪው ቅሬታውን በተለያየ መንገድ መግለፅ የጀመረበት ነው፡ አንዳንድ ሀላፊዎችን እየጠሩ መሳደብ፣ 'ኮሾሮ ይሻላል!' እያሉ ወይ ከመኝታ ዳስ ውስጥ ወይም በእሳት ዙሪያ ሆኖ መጮህ። አንድ ቀን ለምሳ የተሰራው ፓስታ ከመበላሸቱም በላይ ሳይዳረስ በመቅረቱ ተማሪው በሙሉ ሳህኑን ይዞ ወደ ብርጌድ አዝማች ዶ/ር በየነ ጭጭአይበሉ ቤት አካባቢ ሄድን፡ ችግሩን በደንብ ስለሚያውቁት ሁኔታውን በማስተባበል፣ ጩኸትም

እንደማያስፈልግ በመምከር በጥፋተኞቹ ላይም እርምጃ እንደሚወሰድ ገልፀውልን ተመለስን፡ ዶ/ር በየነ ተሰሚነትና ተዓማኒነት ስለነበራቸው ከዚህ ክስተት በኋላ የኡኡታና አመፅ ሁኔታ ቀነሰ።

## ሳምንት 4

እሑድ እለት ማታ የሆድ ቁርጠት ጀምሮኝ ስለነበር በጠዋት ሐኪም ቤት ሄጄ ቦታ ያዝኩኝ፡ የታዘዘልኝን መድሀኒት ይዤ ወደቤት ተመልሼ ሌላ ታሞ ከነበረ ልጅ ጋር አርፈን ዋልን፡ እራሴንና ሆዴን ቢያመኝም ፍቃድ ስለማይሰጥ ወደ ስራ ለመሄድ ብሞክርም አልሆንልኝ ሲል በቀሪነት ተመዝግቤ ቤቴ ዋልኩ፡ ማክሰኞ ሻል ስላለኝ ወደ ስራ ሄድኩ፡ ራስምታቱ ሲመጣ በመቻል አጣዳፊ የሆድ ቁርጠት ሲመጣ ወደ ጫካ በመሄድ አሳልፌ ተመለስኩ፡ በዚህ እለት የተማሪውን ጥያቄ ጠንከር ለማድረግ የምግብ ማቆም አድማ ተደርጎ ስለነበር ቁርስ አልበላንም ነበር፡ ከስራ መልስ (ከምሳ በፊት) ስብሰባ ተጠርቶ አዝማቹ ያለውን ችግር ችግሩን ለመፍታት የተደረገውን ጥረት ዘርዝረው አስረድተውን ወደ ምሳ ሄድን፡ ከዚህን እለት ጀምሮ የተለያዩ የታሸጉና የጣሳ ምግቦች እየተጨመሩ ይቀርቡልን ጀመር፡ ዓይነቱ ጥሩ ቢሆንም መጠኑ በጣም አነሰና አላጠግብ አለን፡ ምግቡንም ለመለማመድ ጊዜ ወሰደብን፡ አንዳንዶች ጭራሽ አይወስዱም (የፈረስ ስጋ ነው ምናምንም ይባል ነበር)፡ ለማንኛውም እነዚህ ምግቦች የሚታደሉት ማክሰኞ ሐሙስና እሑድ ብቻ ነበር። በዚህ ሳምንት መጨረሻ (ቅዳሜ ሐምሌ 20 ጁላይ 27) የምረቃችን ቀን ነበር፡ ከባድ ዝናብም ጣለ፡ ለማ ምትኩ በሙታንቲ የለወጣት አንዲት ዶሮና በአንድ ብር የተገዛ አስር እንቁላል ሰርተን ልንፈነጥዝ ስንሞክር ጎርፍ ቤታችን ውስጥ ገብቶ ያነደድነውን እሳት ሊያጠፋው ሆነ፡ ስራ ተከፋፍለን ግማሹ ጎርፉን ሲያስወጣ ግማሹ ቢላዋና ሌሎች ግብዓቶች ፍለጋ ተሰማራን፡ ዶሮዋ በጥሩ ሁኔታ ተገነጣጥላ ከታጠበች በኋላ በአራት ሽንኩርትና በዘይት ፈንታ በዝግን የጣሳ ወጥ፣ ጨውና በርበሬ ጨምረን ለቦታው የሚመጥን ምግብ ሰራን፡ ዶሮዋ ከተሰራች በኋላ በምን ትበላ? የካፊቴሪያ ምግብ እስኪደርስ ካርታ እየተጫወትን ቆየንና ምሳ ሲታደል ፓስታችንን ይዘን ወደቤታችን መጣን፡ ዶሮዋ እንደ ሱሳ ከላይ ተጨምራ አንዳንድ እንቁላልና ስጋ ደርሶን ተሰብስበን በሙብላት እለቱን ዘከርነው ይባላል። ሌሎች በዝናቡ ምክንያት ምግብ አላጠግብ ሲላቸው እኛ ግን በጣዕምም በመጠንም ረክተን ዋልን፡ ቀሪውን ጊዜ ካርታ ስንጫወት ውለን በማግስቱም እሑድ ስለነበር ጥሩ ዊክኤንድ አሳለፍን፡ በዚህ ላይ ሳምንቱ ቃል በተገባልን መሰረት የዘመቻው ግማሽ መንገድ ነው፡ ምንም የቀን ለውጥ ወሬ አልሰማንም፡ እንደውም ነሐሴ 15 መመለሻችን ሊሆን እንደሚችል ብንሰማም ኮታ ካልሞላችሁ አትሄዱም የሚል ማስፈራሪያም ነበር።

## ሳምንት 5

ገና ከጅምሩ በጥዋቱ መዝነብ ስለጀመረ ወደ ስራ ሳንሄድ ቀረን፡ ክረምቱ እየጠነከረ ስለመጣ ኮታችንን የመሙላት ችግር ተከሰተ፡ 5 ሰዓት ላይ ስብሰባ ሲጠራ 100 ሜትር ያህል በመረሬው ጭቃ ላይ ለመሄድ ላብ ላብ እያለን ደረስን፡ ከቡድን መሪው በተደረገልን ገለፃ በጠቅላላው ለብርጌዱ ከተመደበው የ3500 ቤቶች የፌዝ 1 ኮታ ውስጥ የተሰራው 800 ብቻ መሆኑንና ለዚህ ብዙ ምክንያት ቢኖሩም አንዱ ምክንያት የኛው ድክመት መሆኑን፣ በሁለተኛው ፌዝ ጠንክረን መስራት እንዳለብን አሳሰቡን፡ ከዚህ በፊት እንደ ሐረግና ማገር አይነቶች የምናሚላው እኛ ራሳችን ነበርን፡ አሁን ግን ለዚሁ ስራ የተመደበ ሀይል ስላለ እኛ ግንባታው ላይ ብቻ እንድናተኩር ተደረገ፡ ለወትሮው አንድ ወይም ሁለት ሲቀር ወደቤት የምንሄደው ቀርቶ ቤቱን እስክንጨርስ ለመስራት ሰአት ማሳለፍም ጀመርን፡ ቦታው ከመኖሪያችን 3 ኪሜ ስለሚርቅ በቀን 4 ጊዜ መመላለስ መንገዱ ብቻ ምን ያህል አድካሚ ነበር፡ በተለይ በምሳ ሰዓት በሙቀት ያን ሁሉ መንገድ መጥተን ለምሳ መሰለፍ ከምሳ በኋላ ደግሞ በ9፡30 በዛ ሙቀት ወደ ስራ መመለስ አድካሚ ነበር፡ ለካ ሰው የማይችለው ነገር የለም? ለቅንጦት ሲሆንና የግድ ሲሆን ልዩነቱ ሰማይና ምድር ነው፡ እሑድ እለት ከቁርስ በኋላ አንድ እንግዳ ከኡባላ መጣብኝ፡ ከእንግዳው ጋር ተቀምጠን ሳለን አሳሾች መጥተው ሁላችንም ወደ ስብሰባው እንድንሄድ አረጉን፡ የስብሰባው አላማ ስለጤንነት ጉዳይ ሲሆን ተቅማጥና ትኩሳት ብዙ ሰው እያጠቃ ስለሆነ ለመከላከል መደረግ ያለባቸውን ነገሮች በባለሙያ ምክር ተሰጠን፡ አዝማቻችን ዶ/ር በየነም ተጨማሪ ሀሳብ ከሰጡን በኋላ እንደተለመደው ማሳቅና ማዝናናት ጀመሩ፡ ንግግራቸውን በጣም ስለምንወደው በየደቂቃው ጭብጨባ ነበር፡ አስከተለውም የቀረን ሶስት ሳምንት ብቻ መሆኑንና **"የተራቡ ወገኖቻችንን ለማዳን እኛ መሞት የለብንም!" "ለማንም ቢሆን አልርበደበድም፣ ሹመትም አልፈልግም ብዕር የሾመኝ ነኝና" "አንዳንድ የአይን አገልጋዮች....."** እያሉ በዛ መንግስት በሚ'ፈራበት ዘመን በድፍረት ተናገሩ። ስለ መልስ ጉዟችን ስላረጋገጡልን ግን ተደስተናል፡ እንደውም ከሰማን በኋላ ቀኑ ራቀብን።

እሑድ ከሰዓት በኋላ ዝናብ በመዝነቡ ከቤት ሳንወጣ ዋልን፡ ውሃ ቤታችን ውስጥ በመግባቱ ዕቃዎችን በማሸሽና ውሀ በመከላከል ለመውጣት ጭቃው ስለማያላውስ እስከ ምሽት ቤታችን ውስጥ ቆየን፡ ከእራት በኋላ እንጨት ለቃቅመን በሙታንታ የቀየርነውን የበቆሎ እሸት እየጠበስንና እየተቀላለድን አምሽተን ተኛን።

## ሳምንት 6

ሰኞ ዕለት በጣም ከባድ ጭቃ ቢኖርም ከስራ አልቀረንም፡ በዚህ ሳምንት የሰዓት ለውጥ ተደርጎ ጠዋት በ1፡30 ገብተን እስከ 8፡30 ሰርተን ከዛ በኋላ አንመለስም (አንድ ሽፍት ሆነ ማለት ነው)፡ እንዳይርበን ቁርስ ላይ አንድ ተጨማሪ ቂጣ ይሰጠንና ይዘን እንሄዳለን፡ ስድስት ሰዓት አካባቢ በልተን ውሃ እንጠጣለን (ከሻ ወይም እስናክ ማለት ነው)፡ የመጀመሪያው ቀን ከስራ ስንመለስ አቶ ስዩም የሚባል ለፋፊ በድምፅ ማጉሊያ "ለዘማቾች በሙሉ" በሙሉ ብሎ ጀመረና "የመጀመሪያዎቹ 500 ሰፋሪዎች ከዓርብ ጀምሮ ስለሚመጡ ለነሱ መቀበያ ይሆን ዘንድ የመንደር አንድን ቤቶች በመከደንና ማንኛውንም ቅድመ ሁኔታ ለማሟላት አዲስ የስራ ድልድል ከማክሰኞ ጀምሮ እንደሚኖር ገለጠ፡ በዚህ ድልድልም መሰረት ሳር አጨዳ ደረሰን፡ ሳር አጨዳ በጣም የተጠላ ስራ ነው፡ እንደሌላው ስራ ዕረፍት ካለመስጠቱም ሌላ ሳሩ እጅ መቆራረጡና ገላም መቆጥቆጡ ሳያንስ ለእባብ መሰል አውሬዎች ያጋልጣል፡ ሆኖም ግን ይቺን የቤት ስራ በ6 ሰዓት ውስጥ ጨርሰን ወደቤታችን ተመልሰን ግማሽ ቀን ማረፍ ስላስቻለን ደስ ብሎን ዋልን፡ ሰፋሪዎች ስለሚመጡ ተጨማሪ ቤቶች በሳር ይከደኑ ተብሎ ሳር እያጨድን ከደናውንም (መከፍከፍ) እዛው እየተለማመድን መስራት ተያያዝን፡ ብዙ የቡድናችን አባላት በህመም ምክንያት ከስራ ስለቀሩ ያለማረፍ ሳር ስናጭድና ስንከድን ወገባችን ተንቀጠቀጠ፡ ወደ ሳምንቱ ማለቂያ ይመጣሉ በተባሉት ሰፋሪዎች ፈንታ መጠኑ የበዛ የቤት መስሪያ እንጨት በግዳጅ መኪናዎች ይጋዝ ጀመር፡ ከዚህ በኋላ ዘመቻው ለ15 ቀን ጨምሯል የሚል ወሬ መናፈስ ጀመረ፡ አንዳንዶች እስከ ነሐሴ መጨረሻ እንቆያለን ይላሉ፡ ሌሎች ደግሞ ኮታው ስላልተሟላ መቆየታችን ግድ ነው ይላሉ፡ ግማሹ ግምት ቢሆንም አንዳንዱ ውሸትም ነበር (ዛሬ ፌክ ኒውስ እንደሚባለው 😀)።

ሐሙስ ዕለት ማታ ካምፕ ፋየር ተዘጋጅቶ አዝማቾችን በቀልድ በተሞሉ ንግግራቸው ውስጥ ከ3 ሳምንት በኋላ እንደምንሄድ ሲደግሙልን ወሬ ሁሉ ፉርሽ ሆነ ብለን ተረጋጋን፡ የመንግስት ነገር ግን የማይታወቅና ተለዋዋጭ ስለሆነ ለሁሉም መዘጋጀት ጥሩ ነው።

## ሳምንት 7

በዚህ ሳምንት የዘመቻው መራዘም ወሬ ጋብ ብሎ የመሄጃ ቀናችን ወሬ ጋል ማለት ጀመረ፡ ኮታችንን ለማሟላት መንደፋደፍ ያዝን፡ ለዘመቻው ማስታወሻ ይሆን ዘንድ ፎቶ ለመነሳት ያመጣሁትን ፊልም በካሜራ እጦት ሳልጠቀምበት ቆይቼ ካሜራ በማግኘታችን በየወንዙና በየደኑ ውስጥ ፎቶ ተነሳሳን፡ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ለሳምንታት ስጠባበቅና ሳላገኘው የቀረሁትን ደብዳቤ *(አንዴ ከ300 ደብዳቤ ያላቸው ሰዎች ስም ዝርዝር ውስጥ አለመኖሬ ያሳዘነኝ አይረሳኝም)* ዛሬ ሶስት ኤሮግራም ከቀን እንቅልፌ ስነቃ **ዛንዛሪናዬ** ላይ ተቀምጠው ሳገኝ የተደሰትኩት ከልክ በላይ ነበር፡ ከሶስቱ አንዱን በችኮላ ቀድጄው ኖሮ ግን በኔ በኩል ሌላ ጣቢያ ለሚገኘው የሰፈሬ ልጅ ለግዛው የተላከ ነበር፡ የሳምንቱ መቋጫ ክስተት የቅዳሜ ማታው ካምፕ ፋየርና በጉጉት የምንጠብቀው የዶ/ር በየነ ንግግር ነበር፡ ሲመጡ ሞቅ ባለ ጭብጨባ ተቀበልናቸውና እሳቸውም ዘመቻው የሚያልቀው ነሐሴ 24 በመሆኑ በቀሪዎቹ 12 ቀናት የሁለት መንደር ቤቶች (አንድ ሺ ቤት) ተሰርተው እንዲያልቁ መወሰኑን ሲነግሩን መጨረስ ባንችልስ? በማለት ትንሽ ቅሬታ ውስጥ ገብቼ ነበር፡ በተረፈ ግን ይህ ሳምንት ብዙ ጥሩ ጥሩ ነገሮች የተከሰቱበት ሆኖ አልፏል፡ ለምሳሌ አንድ ቀን ፊልም አይተናል፣ የበሬ ስጋ አግኝተን በልተናል፡ የ10 ብር ስጋ 14 ሆነን ግማሹን ቁርጥ ግማሹን በባልዲ ቀቅለን የበላነው አይረሳም፡ ገና ብዙ ባይሰራጭም ተቅማጥና ትውከት ያለበት በሽታ ተከስቶ ስለነበርና ከቤታችንም የተያዙ ስለነበሩ ላለመያዝ ያደረግኩት ጥንቃቄም አንዱ ክስተት ነበር።

## ሳምንት 8

ሰኛ ዕለት መንደር 3 ተጠናቆ መረከብ ስላለበት የቀሩንን አራት ቤቶች ከፍተኛ ጥረት ይጠበቅብናል፡ ሰኞ ለት አብዛኛውን ነገር ጨርሰን ቀሪውን ማክሰኞ ለመስራት እቅድ ያዝን፡ እንደገና የስራ ሰዓት ለውጥ ተደርጎ ከሰዓት በኋላም ወደ ስራ መመለስ ጀምረናል፡ ሆኖም ግን እንደቀድሞው ሰዓት አይቶ ወደቤት መሄድ ቀርቶ ሰዓት ቢያልፍም ስራው እስኪያልቅ መስራት ተለመደ፡ ለምሳ እንኳን የምንሄደው ምሳ እንዳያመልጠን ስንል ሆነ፡ ረጅም ሰዓት

መስራቱ፣ መንገዱ፣ ምግብ መመገብ አለመቻልና የኮታው ጫና ይብስ አዳከመን፡ ሰኞ ከሰዓት እንደውም የህመም ስሜት ስለተሰማኝ እዛው ስራ ቦታ ዛፍ ስር ተኛሁ፡ ወገቤን ራሴንና ጠቅላላ ሰውነቴን ስላመመኝ ወባ መስሎኝ ሰግቼ ነበር፡ ባልደረቦቼም ወደቤት እንድሄድ ገፋፍተውኝ መንገድ ላይ ትራክተር አግኝቼ (በእግር መሄድ ይሻል ነበር) ወደ ቤት ገባሁ፡ እቤት እንደደረስኩም ልብሴን ቀይሬ ጥቅልል ብዬ ተኛሁ፡ ሽርተቴ፡ ራስ ምታትና ትኩሳት ነበሩብኝ፡ ምግብም ሳልበላ ነበር የተኛሁት፡ በቤቱ ውስጥ 3ኛው ታማሚ መሆኔ ሌሎቹንም አስደነገጣቸው፡ እቤት ውስጥ አንድ ኪኒን ውጬ ተኛሁ፡ በማግስቱም ክሊኒክ ሄጄ ተመረመርኩ፡ የታዘዘልኝን መድሃኒት መውሰድ ከጀመርኩ በኋላ ተሻለኝ፡ ከሰዓት ወደ ስራ ሄድኩ፡ በስራ ላይም ሽርተቴው ያሯሩጠኝ ነበር ግን ጠንክረን ሰርተን ጨርሰን ያንን መንደር ለቀቅን፡ ዕሮብ እለት እስታንድባይ (ተጠባባቂ) ሆነን ውለን ሐሙስ እለት ወደ ሌላ መንደር ተመደብን፡ በህመም ምክንያት አባላት ስለጎደሉብን ስራው በፍጥነት አልሄድ ቢል ረዳቶች ከቡድናችን ተልከውልን ከመንደር 5 ቅዳሜ ጨርሰን ወጣን፡ በዛኑ ዕለት ራቅ ወዳለው ወደ መንደር 4 ሄድን፡ ከርቀቱ የተነሳ ምሳ የሚበላው እዛው በየዛፉ ስር ነበር፡ የሚጠጣ ውሀ ችግር ሆነብን፡ መታጠብማ አይታሰብም፡ በመኪና የሚመጣውን ምሳ ለማግኘት የምንሰለፈው የእረፍት ጊዜያችንን ይበላብናል፡ ያም ሆነ ይህ መስራት ይቀጥል ነበርና ምሳችንን በልተን ከአንድ ቡድን ጋር በረዳትነት መስራት ጀመርን፡ ስራችን የነበረው ሳር አጭዶ በሽክም በማጓጓዝ ጣሪያ መከደን ነው፡ ስራው ማለቅ ስላለበት ዘግይተን ሰርተን አንድ ሰዓት ሲሆን እራት እንዳያመልጠን ተሯሩጠን ደረስን፡ በማግስቱ እሑድ መሆኑን በማሰብም ነበር ረጅም የሰራነው፡ ሆኖም ግን ሰፈር ስንደርስ ነገ እሑድም እንድንሰራ ተለፍፎ ነበር፡ ሌሎች ቡድኖች ግማሽ ቀን ብቻ ሲሰሩ የኛ ግን ሙሉ ቀን ለመስራት ተወሰኖ፣ ምሳም እዛው መጥቶልን ስንኳትን ውለን አስመስጋኝ ውጤት አስመዘገብን፡ ከዩኒት የወጣነው አራት ብቻ ስንሆን የሰራነው ግን የስምንቱንም የሚሸፍን ነበር፡ ወደዛ መንደር ላለመመለስ ስራውን ማጠናቀቅ ነበረብን፡ ሦስቱን ቀን መደዳውን በጣም ስለሰራን ሰኞ ዕረፍት እንዲሰጠን የቡድን መሪያችን ጠይቀን ስለተፈቀደልን አረፍን፡

## ሳምንት 9 (መጨረሻ)

ከዕረፍት መልስ ማክሰኞ እለት የቀረችንን አንዷት ቤት አጠናቀን ወደ ሰፈር ስንመለስ የቡድን መሪያችን አቶ ደስታ እንየው የምስራቹን ለብርጌዱ መሪ እንዳበሰረ ታሞ ወድቆ በእስትሬቸር ወደ ክሊኒክ ተወሰደ፡ ይህች የመጨረሻ የስራ ቀናችን ናት ብለን ብናስብም ዕሮብን ውለን ሐሙስ እና ዓርብ የህብረት ስራ አለ የሚል ወሬ ሰማን፡ ዕሮብ እለት ከቁርስ በኋላ ትንሽ ተኝቼ ቀጥሎ ልብሴን አጣጥቤ ተዘጋጅቼ ቁጭ አልኩ፡ እንደተወራው ምንም የታዘዝነው ስራ ስላልነበር እፎይ አልን፡ ለፋፊው ስዩም "ዘማቾች በሙሉ የስራ መሳሪያዎች፣ ብርድልብስና ሌሎችም ዕቃዎች መልሳችሁ ክሊራንስ እንድታወጡ" ሲል የዘመቻው ፍፃሜ መሆኑን ስናረጋግጥ በደስታ ሲቃ ያዘን፡ አሁን የቀረን ነገር የጉዞውን ቀን ማወቅ ብቻ ነው፡ ከታመኑ ምንጮች እንዳገኘነው ጉዞው የሚጀመረው ነሐሴ 25 ቀን ሲሆን በሶስት ምድብ/ቡድን ተከፍሎ ነው፡ ውሳኔው የተሰጠው በዕጣ ሲሆን ቡድን 1 ቅዳሜ ቡድን 2 እሁድ ቡድን 3 ሰኞ በመሆኑ እኔ ለእሑድ ተዘጋጀሁ፡ ዶ/ር በየነ ይህንኑ ዜና ካምፕፋየር ላይ ሲነግሩን ሞቅ ያለ ጭብጨባ ተቸራቸው፡ በዝግጅቱ ላይም የአኟክ ሙዚቃ ቀረበልን፡ ዓርብ ከሌሊቱ 10 ሰዓት ወደ ታታ (ዋና መ/ቤት እንደማለት ነው) እንደምንሄድ ተነግሮን ተዘጋጀን።

## ቅድመ ጉዞ ዝግጅት

**የታታ ስብሰባ፡** በሌሊት ቁርስ በልተን ወደ ተዘጋጀልን የጭነት መኪና ለመሄድ ስንሞክር በሌሊቱ ዝናብ የተፈጠረው ጭቃ አበሳችንን ያሳየን ጀመር፡ ዝናቡም ያካፋ ነበር፡ የመጀመሪያ ዙር ተማሪዎች ከሄዱ በኋላ ሌላ ዙር መኪና ሲመጣ የቀረነው ተሳፈርን፡ ታታ ላይ ከጋምቤላ አውራጃ በሙሉ ያሉ አስር ሺህ ያህል ዘማቾች በሙሉ ስለሚሰበሰቡ ደስ የሚል ድባብ ይኖራል ሌላ ተቋም ያሉ ጓደኞቻችንንም እናገኛለን ብለን አስበን ነበር፡ ከጊሎ የጀመረን ካፊያና ጭቃ ታታ ስንደርስ በከባድ ዝናብ ተተካ፡ እስከተመለስንበት ሰአት ድረስ ያለማቋረጥ ሲዘንብ የዝናብ ልብስ ያላቸው ለብሰው ወይም ከሌላ ጋር እየተጋሩ ይጠለሉ ነበር፡ ጥላ የነበራቸው ጥቂቶች ሲኖሩ አብዛኞቻችን ዛፍ ስር ወይም ዝናቡ እንደሌለ በመቁጠር ውስጡ መሄድ ተያያዝን፡ ዝናቡም ቅዝቃዜውም ከረሀቡ ጋር ተደራርቦ ፈተነን፡ "አገርህን ዕወቅ" ስለሆነ መቻል ነዋ!! የመጨረሻው ንግግር ሲጀመር ተማሪዎች ጥለው ወደየመኪናቸው ሲሄዱ ወታደር ሊያስቆም ሞክሮ አልተሳካም፡ እኛ ዘግይተን ስለሄድንና መኪናም ገና ስላልነበረን እዛው እንደቆምን የባሰ ዝናብ ወረደብን፡ ከብዙ ስቃይና ግርግር በኋላ መኪና አግኝተን ወደ ሰፈራችን ተመለስን፡ መኪናው ላይ የረጠበ ልብሳችን ንፋስ ሲነካው ቅዝቃዜው ና የመኪናው መናጥ እያሰቃየን ነበር የደረስነው፡ መሬት ላይ ጭቃውም ይታገለናል፡ ከምሳ

በኋላ ተኝቼ ስነሳ ደብዳቤ አግኝቼ ደስ አለኝ፡ ምሽቱን እንደተለመደው ስንጫወት አሳለፍን፡ ቅዳሜ ጠዋት ቁርሴን ሰው ነበር ያመጣልኝ።

ቅዳሜ ይነሳሉ የተባሉትም ስለመነሳታቸው ምንም ፍንጭ አልታይ አለ፡ በስተመጨረሻ የገጠመን ፈተና መጀመሪያ ላይ ቢሆን ኖሮ እንዴት እንዘልቀው ነበር? ዕቃዎቻችንን ስላስረከብን የመጠጥ ውሃ ችግርም ገጠመን፡ ቅዳሜ ማታ ስብሰባ ተጠርቶ ስለ ጉዞው ማብራሪያና ስለ ሽልማት ተወራ፡ "ታታ ላይ ተቋርጦ የነበረው በዓል ጋምቤላ ከየብርጌዱ በተወከሉ ሰዎች ቀጥሎ በብርጌዶች ውድድር ብዙ መታየት የነበረባቸው መስፈርቶች ሳይካተቱ መድልዎ ባለበት ሁኔታ በተደረገው ምርጫ የኛ ብርጌድ ሳያሸንፍ መቅረቱና የአሰራሩ ብልሹነት አበሳጨን፡ ሆኖም ግን የብርጌድ አዝማቾችን የፀባይ ዋንጫና የወርቅ ሰዓት ለአመራር ብስለታቸው መሸለማቸውን ስንሰማ ተፅናናን በከባድ ጭብጨባ ደስታችንን ገለፅን።

ስለጉዞው ግን ዶክተሩም የሚያውቁት ነገር እንደሌለ ነገሩን፡ መኪና ስንጠባበቅ ቀናት ተቆጠሩ፡ እግረመንገዳችንን ቀሪ የግል ዕቃዎቻችንን በተለያዩ ነገሮች ስንቀይር ቆየን (ገንዘብ አይታወቅም - ባርታር ሲስተም ነው የሚወዱት፡ ለነገሩ ሸቀጥ ከሌለ ገንዘቡ ምን ያደርግላቸዋል?)፡ እሑድ ልክ የእራት ሰዓት ላይ 9 አውቶቡሶች መድረሳቸው ተሰምቶ ፈንጠዝያ ሆነ፡ ማታውኑ እቃዎች ተጭነው ሰኞ በሌሊት የመጀመሪያው ቡድን ተነሳ፡ አሁን ቁርጥ ሲሆን ሰኞ እለት እቃዎቻችንን በተለይ የደከሙ ልብሶችና ጫማ መሸጡን አጧጧፍነው - ለመንገዳችንም ሳንቲም ያስፈልገን ነበርና። ጊሎን ለመጨረሻ ጊዜ ተዘዋውረን ተሰናበትንና ለማክሰኞ ጉዞ ተዘጋጀን፡ ነሐሴ 28 (SEPT 2) ከአራት ቀን በኋላ (ጳጉሜ 1) አለማያ የምንገባበት በምናብ እየታየን በሽታውና ድካሙ ተረሳ፡ የመሰናበቻ ፓርቲ ለማድረግ ፍየል ለመግዛት ብናስብም በጣለው ከባድና ነፋሻ ዝናብ ሊረብሸን ሞከረ፡ ዝናቡ እንደቆመ ፍየል የሚገዙት ወደ መንደር ተልከው እኛ ዕቃ ማደራጀት ያዝን፡ አንድ ወጠጤ ተገኝታ እቃ ከዚም ከዚያም ተፈልጎ ቅቅል በባልዲ ተጣደ፣ የደም ጥብስና ድሎትም ተዘጋጀ፡ የተዘጋጀውን በኮሾሮ ቀማምሰን ተኛን።

## የመልስ ጉዞ

ከሌሊቱ በ9፡30 ወደ መኪናችን ገብተን በ11 ሰዓት ጉዞ ተጀመረ፡ ያቺን የብዙ ትዝታዎች ካዝና የሆነች መንደር በጭለማም ቢሆን አየቃኘን መሳደብም እየቃጣን በደስታ ተውጠን እየተሳሳቅን የቀናት ጉዞአችንን ጀመርነው፡ በመጀመሪያ የደረስነው ጋምቤላ ከተማ ሲሆን ድልድዩን ብቻ አሳይተውን ('ባሮ አለፈልሽ!') ወጥተን ጉዞ ቀጠልን፡ የኛ መኪና (ሎንቺና) ውስጥ ሙዚቃ አለመኖሩ ቢያሳዝነኝም ይሄ ቅንጦት ስለሆነ ብዙም አላስቸገረን፡ ጥቂት ሰዓታት ተጉዘን እያረፍን መንገድ ቀጠልንና የመጀመሪያው ከተማ ቡሬ ላይ ስንወርድ፡ ህፃናት ሲሯሯጡ፣ ሆቴል ባር ማየት ብርቅ ሆነብን፡ ኮሾሮና ዝግን ወጡን እየተመገብን ነበር የምንጓዘው፡ ሌሎች ትንንሽ ከተሞች (እነ ጉሬን) አልፈን መቱ ስንደርስ 11 ሰዓት ሆኖ ነበር፡ ከጋምቤላ እስከ መቱ ያለው መንገድ ገደላገደል ስለነበር ያስፈራ ስለነበር መኪኖቹ በቀስታ ነበር የሚጓዙት።

መቱ የወረድነው ለአዳር ሲሆን የምናርፈውም አንድ አጠቃላይ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ውስጥ ነበር፡ ወለል ላይ ስሌኖች ተነጥፈው ቦታ ቦታችንን ያዝን (ከዘመቻ ለመጣ ይህ ምንም ችግር አይደለም ነበርና)፡ ዘወርወር ለማለት ስወጣ የቀበሌዬን ልጅ ሳምሶን ከበደን ባልጠበቅኩት ቦታ ሳገኘው ደስ አለኝ፡ ከሱ ጋር ሆነን ከዘመቻው ወዲህ ለመጀመሪያ ጊዜ እንጀራ በልተን ለመበተኛም አልኮል ጠጣን፡ የተዘጋጀልንን ኮሾሮ በሻይ ንቀን ተውነው፡ በሚቀጥለው ቀን በጠዋት ተነስተን እሽቅድምድም የሚመስል ጉዞ ጀመርን፡ የኛ መኪና ደግሞ ደከም ያለ ስለነበር ብዙ መኪና አልፎን ሄደ፡ ይባስ ብሎ በደሌ ልንደርስ ትንሽ ሲቀረን ጎማ ፈንድቶ 30 ደቂቃ አዘገየን፡ በዴሌ ስንደርስ ሌሎቹ መኪኖች እኛን መጠበቅ ሰልችቷቸው ሊንቀሳቀሱ ሲሉ ነው የደረስነው፡ የኛ መኪና ጋራዥ ገባና ከአንድ ሰዓት በላይ በዴሌ ውስጥ ቆየን፡ የኛ ምኞት በጊዜ ጅማ ገብቶ ከተማውን ለመጎብኘት ቢሆንም ሳይሳካ ቀረ፡ በዴሌ ውስጥ ከታዘብነው ነገር ውስጥ አንዱ የለማኝ ብዛት ነበር፡ የሚበላ ሰው ሲያዩ ከቶ ንጥቂያ ነው የሚቀራቸው፡ ከ6 ሰአት በኋላ ከበዴሌ አጋሮ ስንደርስ አሁንም ጋራዥ ገብቶ አንድ ሰአት ተቃጠለ፡ ንዴትም ተስፋ መቁረጥም ያዘን፡ ከተማውን ትንሽ አይተን ማምሻውን ጅማ ገባን፡ የቀደሙን ዘማቾች ሲገቡ ደማቅ አቀባበል ተደርጎላቸው፣ ኪነት ሙዚቃ ተጋብዘው፣ ከተማውን ተዘዋውረው አይተው ወደ ማረፊያ ሲገቡ ነው እኛ የደረስን፡ ያለችንን ጊዜ ቶሎ ለመጠቀም ወጥተን ከጓዶኞች ጋር ወጣ ብለን እራት በልተን በየባሩ እየተዝናናን ሳለ ዝናብ ደግሞ መውረድ ጀመረ፡ ዝናቡ እንዳቆመ ወዳረፍንበት TTI ኮሌጅ ሄደን ዶርም ውስጥ ስላደርን በጣም ተመቸን፡ በማግስቱ 12 ሰዓት አካባቢ ከጅማ ተነስተን

በተረጋጋ ጉዞ ያካባቢውን መልክዓ ምድር እነ ጊቤ ወንዝን ጨምሮ እያየን ሙዚቃ እየኮመኮምን ግማሹ ጫት እየቃመ አዲስ አበባ ገባን፡ ይህንን መስመር ለመጀመሪያ ጊዜ ማየቴ ነበርና ሜዳማነቱ መሰጠኝ።

አዲስአበባ እንደገባን በአጃቢ መኪናዎች እየተመራን በከተማ ውስጥ እያለፍን እያለ የኛ ጣጠኛ መኪና ተበላሽቶ ከሰልፉ ወጥቶ ቆመ፡ ደግነቱ ቶሎ ተጠግኖ ተነሣ፡ በዚሁ መሀል አንድ ከአለማያ አምና የተመረቀ ልጅ አግኝቼ ከኛ ጋር ሊያመሽ ወደ ማረፊያችን አብሮኝ ቢመጣም "እራት በልታችሁ ሌሊቱን በባቡር ወደ ድሬዳዋ ትሄዳላችሁ" ተባልን፡ ግዛውንም አግኝቼው አብረን ምሽት አራት ሰዓት ላይ እራት እንዳለቀ ወደ ባቡር ጣቢያ ሄደን ባገኘንበት ገደም ገደም ብለን ስንጓዝ አደርን፡ አዋሽ ስንደርስ ነግቶ ነበርና ባቡሩ ሲቆም ቁርስና ሻይ ብለን ጉዞ ቀጥለን ወደ 7 ሰዓት አካባቢ ኤረር ደረስን፡ ኤረር ብዙ አቆይተውን ድሬዳዋ ስንደርስ ባልስልጣናት ኪነት ህዝቡ በጭብጨባ ሲቀበሉን ስናይ ከጦር ሜዳ እንደመጣ ጉሮ ወሸባ አይነት ስሜት ተሰማን፡ ለአዳር ወደ ቤት ሄጄ በማግስቱ ከተማሪዎቹ ጋር ወደ አለማያ ሄድኩ፡ ባቴ ጨለምለም ሲል ስንደርስ በችቦና በእልልታ የታጀበ ደማቅ አቀባበል ተደረገልን፡ አቀባበሉ የዘመቻውን አበሳ የሚያስረሳ ወይም የሚያካክስ ነበር፡ ለ2 ወር የተለየነው ት/ቤታችንን ማየት ስሜት ይኮረኩር ነበር።

አሑድ እለት (ጳጉሜ 3 ቀን) በሙዚቃ የታጀበ የራት ግብዣ ተደረገልን፡ ቁርጥና ቢራ ሳይቀር የነበረበት እራት ስለነበር በጣም ተደሰትን፡ በማግስቱ ድሬዳዋ ቤተሰብ ጋ ከተቀላቀልኩ በኋላ ለሚጠይቀኝ ሁሉ ስለ ጋምቤላ ህይወት እየተረኩ አሳልፋለሁ፡ ለማንኛውም ያየነውን ካየን በኋላ እቤት ውስጥ ከቤተሰብ ጋር ማሳለፉ ራሱ ደስታን ይሰጠኝ ነበር፡ የመስራት ፍላጎቴ ጨምሯል - መስራት እንደምችልም ጋምቤላ ስላስተማረኝ፡ እንዲህ እንዲህ ብሎ ቀናት አልፈው የዕረፍት ጊዜ አልቆ ወደ ኮሌጅ መመለስ - መማር፣ ማጥናት፣ መፈተን፣ ካፌቴሪያ መሰለፍ - ማሰብ ከበደን።

**<u>ስንመለስ ያለፍንባቸው ከተሞች</u>**

ከጊሎአቦል - ጂካዎ - ኢታንግ - ጋምቤላ - ቡሬ - ጎሬ - መቱ - ሁሩሙ - በዴሌ - አጋሮ - ጅማ - ወልቂጤ - ወሊሶ - ቱሉቦሎ - ሰበታ - አዲስ አበባ - አቃቂ - ዱከም - ደብረዘይት - ሞጆ - ናዝሬት - ወሊንጪቲ - መተሀራ - አዋሽ - ሚኤሶ - -  - -- ድሬዳዋ - ደንገጎ - አዴሌ - አለማያ - ባቴ

## ትምህርት ከዘመቻ መልስና ምረቃ

የተመደበልን የትምህርት ጊዜ ሶስት ሳምንት ብቻ ሲሆን አንድ ሳምንት ደግሞ ለፈተና በድምሩ አንድ ወር መሆኑ ነው፡ ትምህርት ከጀመርን በኋላ የጥናት ሙድ ውስጥ መግባት በጣም አስቸገረን፡ ሳናስበው ቀኑ እየሮጠብን ሲሄድ በጫቱም በቡናውም ብለን ኮስተር ያለ ጥናት ጀመርን፡ ገንዘባችንን አንድ ላይ ሰበሰብንና (በራስ 10 ብር) ያለውን ገንዘብ ባሉት ቀናት አካፍለን በቀን ወደ 3 ብር ለ5 ሰው የሚበቃ አረንጓዴውና ሻይ እንዲችል አደረግን፡ ከምሳ በኋላ ቶሎ ወደ ዶርም ሄደን እንፈርሻለን፡ ሙዚቃ ስለሌለን እስክንመረቅን ድረስ መበሻሸቅ መቀላለድና አንዳንድ ወሬዎችን ይዘን እንሟገታለን፡ ታዲያ ችግሩ ወሬውን አቁሞ ወደ ጥናት መግባት ላይ የተለያየን ሆንን፡ እንደ ህግ ግን 8 ሰዓት ሲሆን ጥናት ይጀመራል፡ ቀን ቀን በዚህ አይነት ሁኔታ ሲያልፍ የማታው ጉዳይ ችግር ፈጠረ፡ ቀን አጥንቶ ማታም ጥናት ስለሚሰለች ማታ ላይ ወይ የምርምር ሪፖርት መፃፍ ወይም ትንሽም ቢሆን አዝናኝ ነገር መፈለግ፡ ምሽት ላይ ሁሉም በየፊናው የመረጠውን ያደርጋል፡ እኔም ወደ  ባቴ ወይም ግቢ ውስጥ ላውንጅ ለቲቪ እሄድና ስመለስ ወፍራም እንቅልፍ ለጥጣለሁ።

ሁሉም አልቆ ውጤትም ወጥቶ የምረቃችን ቀን ለኅዳር 5 መወሰኑን ስንሰማ ህልም ዕውን ሲሆን ታየን!

## The rest is history!!